2021–2022 መመሪያ

# ቅድመ መዋእለ ህፃናት መግባት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Maryland

## አስቀድሞ መግባት

ቀደም ብለው ወደ መዋእለ ህፃናት እንዲገቡ የሚደረጉ ልጆች ከእኩዮቻቸው ከሚጠበቀው በላይ ችሎታ ኖሯቸው አስቀድሞ ትምህርት መጀመር እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ትምህርት የመቅሰም ችሎታና ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ ዕድገት ማሳየት አለባቸው። ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ በመመደባቸው ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማረጋገጥ አስቀድሞ ለመግባት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ከፍ ያሉ ናቸው። የተወለዱበት ቀን ከኦክቶበር 15 ባሻገር ለሆኑ ልጆች፣ የማመልከት ሂደትን ጨምሮ፣ ምንም የተለየ አስተያየት አይደረግም።

መዋእለ ህፃናት/Kindergarten—በሴፕቴምበር 2 እና ኦክቶበር 15 መካከል 5 አመት እድሜ የሚሞላቸው ልጆች ወደ መዋዕለ ህፃናት አስቀድሞ ለመግባት ተቀባይነት የማግኘት ብቃት ሊኖራቸው ይገባል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ (MSDE) COMAR 13A.08.01.02 እና የሞንትጎመሪ ካዉንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ Policy JEB ይመልከቱ። ወደ ቅድመ መዋእለ ህፃናት፣ መዋእለ ህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል አስቀድሞ መግባት እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ/Regulation JEB-RB፣ ወደ ቅድመ መዋእለ ህፃናት፣ መዋእለ ህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል አስቀድሞ መግባት የሚለውን ይመለከቷል።

## ቅድመ መዋእለ ህፃናት መግባት

### የመዋእለ ህፃናት ፕሮግራም ምን ምን ያጠቃልላል?

የ MCPS መዋእለ ህፃናት ፕሮግራም የተማሪዎችን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ እና የሒሳብ ብቃትን በሚያዳብር ሥርዓተ ትምህርት (ከሪኩለም) ላይ የተመሠረተ ሲሆን ለሁሉም ተማሪዎች ጠንካራ የትምህርት ተሞክሮዎችን ይሰጣል። ይህ ጠንካራ የትምህርት ፕሮግራም የሚያተኩረው፦

- በየእለቱ ማንበብ/መጻፍ/የቋንቋ ስነጥበብ ምድብ
- በየእለቱ የሂሳብ ምድብ
- በየወቅቱ ግስጋሴን የመከታተል ግምገማ እና ለቀጣይ ትምህርት ዝግጅት ማድረግ
- በአነስተኛ ቁጥር- እና ብዙ ሆነው-በቡድን መማር፣ እና
- ራስን ችሎ/ለብቻ የመማር እድሎችን ያካተተ ነው።

የትምህርቱ ፕሮግራም በተጨማሪ ሳይንስ እና የማህበራዊ ጥናቶችን ይዘት ያካትታል፣ እንዲሁም ተማሪዎች በስነጥበብ ሥራ፣ በሙዚቃ፣ በኢንፎርሜሽን ትምህርት፣ እና በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርቶች እንዲሳተፉ እድል ይፈጥራል።

ለተጨማሪ መረጃ፦ እባክዎን የአካባቢዎን ት/ቤት (ሆም ስኩል) በመገናኘት የመዋእለ ህፃናት ትምህርት ክፍል ለመጎብኘት ቀጠሮ ያድርጉ።

## ቅድመ መዋእለ ህፃናት መግባት የተሻለ አማራጭ ነው ወይ?

### እባክዎን የሚከተሉትን ያገናዝቡ፡-

- ቅድመ መዋእለ ህፃናት የመግባት አላማ በ MCPS በሚከናወኑ ግምገማዎች አለካክ መሰረት፣ ከአማካይ በላይ አፈፃፀምና እድገት የሚያሳዩ ለጋ ህጻናት ወደ መዋእለ ህፃናት እንዲገቡ ለማስቻል ነው። የልጁ/የልጅቱ ትምህርት የመቅሰም ክህሎቶች እና ማህበራዊ/ስሜታዊ እድገት ግምት ውስጥ ይገባሉ።
- እነዚህ በእድሜ አነስተኛ ልጆች በመማርያ ክፍል ውስጥ በአንድ አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሚበልጧቸው ልጆች ጋር አብረው መስራት መቻል ይኖርባቸዋል።
- ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ በመመደባቸው ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማረጋገጥ አስቀድሞ ለመግባት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ጠንካራ ናቸው።
- ት/ቤት አስቀድሞ መግባት ወላጆች/አሳዳጊዎች ለልጃቸው የሚያደርጉት የረጅም ጊዜ ውሳኔ ነው። በኤሌሜንታሪ፣ መካከለኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እና ከዚያም ባሻገር በሚያልፉበት ወቅት በልጁ/በልጅቱ ማህበራዊና/ስሜታዊው ሁኔታ ላይ ምን አይነት እምቅ ተፅእኖ እንደሚያስከትል መተንበይ አይቻልም።
- ቅድመ መዋእለ ህፃናት መግባት የልጆች እንክብካቤ መተኪያ ማለት አይደለም። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጅ እንክብካቤ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል፡- በአካባቢያቸዉ ፈቃድ ያላቸው የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር ለማግኘት በ 877-261-0060 ወይም http://www.marylandfamilynetwork.org/programs-services/locate/ ይጠይቁ።

## ለምንድነው ቅድመ ምዋእለ ህጻናት የሚገቡትን አመልካቾች ከሌሎች መዋእለ ህፃናት ገቢ ልጆች ተለይተው ግምገማ የሚደረግላቸው?

በሜሪላንድ ስቴት ደንብ (COMAR 13A.08.01.02) መሠረት፥ ሴፕቴምበር 1 ላይ ወይም ቀደም ብሎ 5 ዓመት እድሜ የሚሞላቸው ልጆች መዋእለ ህፃናት እንዲገቡ የዕድሜ ብቃት ይኖራቸዋል። በስቴት መመርያ መሰረት፣ የልደት ቀኑ/ኗ በሴፕቴምበር 2 እና በኦክቶበር 15 መካከል የሆነ/ች ልጅ ወደ ቅድመ መዋእለ ህጻናት እንዲገባ/እንድትገባ ሊታሰብ ይችላል። የልደት ቀናቸው ከኦክቶበር 15 በኋላ ለሆኑ ልጆች ምንም የተለየ አስተያየት አይደረግላቸውም። የልጅ ትውልድ ቀን ከኦክቶበር 15 በኋላ ከሆነ የማመልከት ሂደት አይኖርም።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ያልደረሰ ጨቅላ ህጻናት ልጆች ቀድመው ወደ መዋእለ ህጻናት ለመግባት ከአማካይ በላይ የሆነ ብቃት ማሳየት አለባቸው። ለቅድመ የልጅነት እድገት ግምገማ ልጆች ማጥናት ወይም ዝግጅት ማድረግ አያስፈልጋቸውም። ግምገማዎቹ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የእድገት ሁኔታዎች የእያንዳንዱን ልጅ አፈፃጸም የሚለኩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላሉ፡ -

- የአእምሮ እድገት
- የንባብና የቋንቋ ስነ ጥበብ እድገት
- የስሌት (ሂሳብ) ትምህርት አስተሳሰብ

## ከማጣሪያው ሂደት ምን ሊጠበቅ ይቻላል?

አስቀድመው ወደ መዋእለ ህጻናት ለሚገቡ ልጆች በሙሉ ከጁላይ 6 እስከ ኦገስት 13, 2021 መመዘኛዎች ይካሄዳሉ። ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው በቨርቹወል ምዘና ላይ እንዲሳተፍ-እንድትሳተፍ ወይም ፊት ለፊት በአካል ምዘና ላይ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ የማድረግ አማራጭ ይኖራቸዋል። ትምህርት ቤቶች ምዘናዎችን የማካሄድ ቀጠሮ ለማስያዝ ከወላጆች/ከሞግዚቶች ጋር ይገናኛሉ። እያንዳንዱ ልጅ ለመገመገም የሚችለው/የምትችለዉ አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ምዘና በሚካሄድበት ጊዜ ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው ጤነኛ እንደሆነ(ች) እና በምዘና ተግባር መሳተፍ እንደሚችል-እንደምትችል የሚገልጽ ቅጽ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ልጆች በምልመላ እና በእንቅስቃሴዎች ላይ

ከመግተፋቸው በፊት ወላጆች/ሞግዚቶች ስለ ቅድመ ትምህርት የመግባት ሂደት ለልጃቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። መሳተፍ ማለት ለመጪው የትምህርት ዓመት ወደ መዋእለ ህጻናት በቀጥታ ያስገባዋ(ታ)ል ማለት እንዳልሆነ ልጃቸው እንዲያውቅ/እንድታውቅ መርዳት አለባቸው። ምዘናዎች የሚካሄዱት በ MCPS ሠራተኞች አማካኝነት ነው። ልጆችም ሆኑ ሠራተኞች ጤንነታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለእያንዳንዱ ልጅ የየራሱ(ሷ) የምዘና ዕቃ ይሰጣል።

ቨርቹወል ምዘና የሚወስዱ ልጆች ለምዘና ከመመደባቸው በፊት ወላጆች/ሞግዚቶች ልጆቻቸው ከትምህርት ቤት የምዘና ቁሳቁስ የሚወስዱበትን ጊዜ ቀጠሮ መያዝ ያስፈልጋቸዋል። ፊት ለፊት በአካል ምዘና የሚሰጣቸው ልጆች ምዘና በሚካሄድበት ወቅት ወላጆች/ሞግዚቶች ላይገኙ ይችላሉ። ት/ቤቱ መቆያ ቦታ ያዘጋጃል።

ቨርቹወል ምዘና ላይ የሚሳተፉ ልጆች ወላጆች/ሞግዚቶች ልጆች በምዘና ላይ በሚሆኑበት ሠዓት ልጃቸው ለምዘና ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ሊረዷቸው አይችሉም። እርዳታ መስጠት የልጁን-የልጅቱን የምዘና ውጤት ውድቅ ያደርገዋል።

ውጤቶቹ በፈተናው እለት አይገለጹም። የት/ቤቱ ቡድን የግምገማውን አሃዞችና መረጃ ድህረ እይታ ያደርጉበታል እናም ከግምገማው በኋላ በ15 ቀናት ውስጥ ከውሳኔአቸው ጋር የፅሁፍ ማስታወቂያ ይሰጣሉ። ልጃቸው ቅድመ ትምህርት ላይ እንዲገባ/እንድትገባ ይሁንታ ካገኘ(ች) በትምህርት ቤት አማካይነት ለወላጅ/ለሞግዚት ይገልጻል።

## ወደ መዋእለህጻናት አስቀድሞ ለማስገባት አንድ ወላጅ/አሳዳጊ እንዴት ማመልከት ይችላል?

- ልጃቸው ወደ የትኛው የአካባቢ MCPS ት/ቤት እንደሚገባ/እንደምትገባ መጀመሪያ ወላጆች/ሞግዚቶች ማወቅና መወሰን አለባቸው። እርስዎ የሚኖሩበትን አካባቢ የሚያገለግለውን ት/ቤት ለማወቅና የክልል መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር፦ 240-314-4700፣ ከ 9:00 a.m. እስከ 12:00 p.m ከሰኞ - ዓርብ ይደውሉ። በተጨማሪ በ MCPS ድረ-ገጽ የሚገኘውን የት/ቤት ምደባ በ www.montgomeryschoolsmd.org፣ የት/ቤት ምደባ መፈለጊያ ቱል/መገልገያ መጠቀም ይችላሉ። የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy JEA፣ Residency, Tuition, and Enrollment ይመልከቱ።
- ከዚያም ወላጆች/ሞግዚቶች ወደ ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለማስገባት (MCPS Form 271-6 መዋእለ ህጻናት ቀድሞ ማስገቢያ ማመልከቻ/Application for Early Entrance to Kindergarten ሞልተው ለልጃቸው ሆም ስኩል ማቅረብ አለባቸው።
- መልከቻውን ከሚከተሉት ቦታዎች ማግኘት ይቻላል፡-
  - የአካባቢ ትምህርት ቤት (ሆም ስኩል)
  - የ MCPS ድረ-ገጽ http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/271-6.pdf
- ወላጆች/ሞግዚቶች ተጠናቆ የተሞላ ማመልከቻ ለልጃቸው ሆምስኩል ማቅረብ አለባቸው።
- ማመልከቻዎችን ከፌብሩዋሪ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ እንቀበላለን።

## ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ት/ቤት ውሳኔ ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

- ስለ ት/ቤቱ ውሳኔ ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የማጣርያ ውጤቶችን ሊወያዩባቸውና ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ ለመጋራት ከት/ቤቱ ርእሰመምህር ጋር ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ።

## ህዝባዊ ላልሆኑ (አማራጭ) እና የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች የስቴቱ መመርያዎች ምንድን ናቸው?

- በ MSDE ደንቦች መሰረት፣ ልጆች መዋእለ ህፃናት ለመግባት እድሜ ብቁ ለመሆን ከሴፕቴምበር 1 በፊት 5 አመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም በእድሜ ብቃት ህፃናት ወደ ነርሰሪ ት/ቤት ለመግባት ሴፕቴምበር 1 ላይ 3 አመት ወይም 4 አመት መሆናቸዉን/እንዲሆኑ ደንቡ ይጠይቃል።

## ተጨማሪ የመዋእለ ህፃናት ፕሮግራም መረጃ የት ይገኛል?

ስለ መዋእለ ህፃናት ስርአተ ትምህርት እና ከፕሮግራሙ ምን እንደሚጠበቅ ዝርዝር መረጃ፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች በ MCPS ድረገጽ Kindergarten Information & Resources (የመዋእለህፃናት መረጃዎችና መገልገያዎች ገፅ መመልከት ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/enroll/Kindergarten.aspx

የሜሪላንድ ስቴት ከሪኩለም ከመዋእለ ህፃናት ምን እንደሚጠብቅ ለመመልከት የ MSDE ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- http://www.mdk12.org/instruction/commoncore/index.html

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሃረግ፣ በብሔርተኝነት፣ በብሔራዊ ማንነት፣ በዜግነት፥ በኃይማኖት፥ በስደተኝነት ሁኔታ፣ በፆታ፣ በጾታ መገለጫ፣ የፆታዊ ስሜት መገለጫ፣ የቤተሰብ መዋቅር፣ የወላጅ ሁኔታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በችሎታ፣ በእድሜ፣ በማኅበራዊ ስሜታዊነት እና በአካላዊ ሁኔታ፣ በድህነት እና በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ወይም ሌሎች በሕግ ወይም በህገመንግስት የተጠበቁ/የተከበሩ ባህሪያትን መብቶች ወይም ትውፊቶችን ጨምሮ ማናቸውንም ሕገ ወጥ መድሎን ይከለክላል። ስለ MCPS ፀረመድሎአዊነት አቋም ሙሉውን መግለጫ፣ ከመመሪያዎች እና ስለ አድሎአዊነት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ፣ ወይም መሰናዶዎችን ለመጠየቅ የግንኙነት መረጃ በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል። http://www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination/።

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*
ህትመት፡- Department of Materials Management for the Elementary Integrated Curriculum Team
0492.21ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 5/21 • NP